EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

ከተማዋን ከትምባሆ ጭስ ነፃ የማድረግ ውጤታማ ክንውን

ትምባሆ አጫሽነት ወይም ተጠቃሚነት በዓለም ላይ በየዓመቱ ከ8 ሚሊዮን በላይ ሰዎችን ለሞት ከሚዳረጉ ትልልቅ የሕዝብ ጤና ችግሮች ውስጥ አንዱ ነው። መረጃዎች እንደሚያመላክቱት በትምባሆ ጭስ ተጠቃሚነት ምክንያት ከሚሞቱት ሰዎች ውስጥ ከ7ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት በቀጥታ ትምባሆን የሚያጨሱ ሲሆኑ ከ1 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት ደግሞ ለጭሱ በተለያየ መንገድ የሚጋለጡ ናቸው።

በማንኛውም መንገድ ትምባሆን ማጨስ እና በየትኛውም ደረጃ ለትምባሆ ጭስ መጋለጥም ሆነ ማጨስ አደጋው አስከፊ ነው። በኢትዮጵያም ይህ ታሳቢ በማድረግ ከተሞችን ከትምባሆ ጭስ ለመከላከል የተለያዩ ተግባራት በመከናወን ላይ ናቸው።

በዘሬው እትማችንም አዲስ አበባ ከተማን ከትምባሆ ጭስ ነፃ ለማድረግ እየተከናወኑ ያሉ ስራዎችን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ከወይዘሪት ሄራን ገርባ ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።

ዋና ዳይሬክተሯ ከተማዋን ከትምባሆ ጭስ ነፃ የሚያደርገው ኢንሼቲቪ ሃሳቡ እንዴት መጣ እንዴትስ እየተከናወነ ነው? በሚል ለተነሳላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ እንደገለጹት የኢንሼቲቩ መነሻ ጥር 2011 ዓ.ም የወጣው አዋጅ 1112/11 ነው። ይሄ አዋጅ ልዩ የሚያደርገው የምግብና የመድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቢሆንም በጣም በተለየ ሁኔታ ጠንካራ ሆኖ ወጥቷል። ትምባሆ ቁጥጥር ድንጋጌዎች ላይ የተቀመጡ ከ«framework convention for tobacco control »ከተባለው ዓለም አቀፍ ስምምነት ታሳቢ ያደረጉ አንቀጾች ወይም ድንጋጌዎች የወጣም ነው።

የሚጨስባቸው ቦታዎችን መከለል ቀደም ሲል የተፈቀደ ነበር። አሁን ግን የተከለለ የማጨሻ ቦታ የሚባሉት ነገሮች ተከልክሏል። የትምባሆ ገላጭ ጹሑፎችም ወይም ፓኬጂንግ በተመለከተ ደግሞ ለውጦች ተደርገዋል። ከዚህ ቀደም 30 በመቶ ብቻ

የነበረው የጤና ጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ወደ 70 በመቶ ከፍ እንዲል ተደርጓል። ከ21 ዓመት በታች ላሉ ወጣቶች ወይም ልጆች ትምባሆ መሸጥም ሆነ እነሱ እንዳይሸጡ የሚያደርግ ድንጋጌዎች ተቀምጠዋል።

አዋጁ ጠንካራ ሆኖ መውጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከማስፈጸም አንፃር በጣም ጠንከር ያሉ ከዚያ ተከታይ የሆኑ የሕግ ማዕቀፎች መውጣት አለባቸው። አብዛኛዎቹ ደግሞ የሚፈጸሙት በክልል ተቆጣጣሪ አካላት ነው። ስለዚህ የክልል ተቆጣጣሪ አካላት አቅም በሰው ኃይል በበጀት በመሳሰሉት ሊጠናከሩ ይገባል።

በየጊዜው አፈጻጸሙን እንከታተላለን። ከክልሎች ጋርም ግምገማ እናካሂዳለን። በተመለከትነው ሂደት ውስጥ ከፍተኛ አመራሮች ተሳትፎም ጥሩ ነው። የትምባሆ ቁጥጥር በአንድ ተቋም ብቻ የሚሰራ አይደለም። ባለስልጣን መስሪያ ቤታችን አንዱ ተግባርና ኃላፊነት የትምባሆ ቁጥጥር ስራን ማስተባበር ነው። በጣም ብዙ አካላት የቁጥጥሩ ውጤት አስተዋጾ አላቸው።

ለምሳሌ የመንግሥት ተቋማት በሙሉ ከትምባሆ ጭስ ነፃ መሆን አለባቸው። እንደዚህ አይነት ተግባራት በጋራ የሚተገበሩ ናቸው። ይሁንና ከተቋማት ከፍተኛ አመራሮች ጋር የአዋጁን አፈጻጸም ስንገመግም አጥጋቢ አይደለም። በየጊዜው ግን ሪፖርት ይቀርባል።

አዲስ አበባ የኢትዮጵያም ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ መዲና ጭምር በመሆኗ ትልልቅ ዓለም አቀፍ ተቋማት አሉ። የብዙ ዲፕሎማቲክ ማሕበረሰብ የሚኖርበት ትልቅ ከተማ ናት። ይሄን መሰረት አድርጎ ከተማው ላይ በተለየ ሁኔታ ብንሰራ ለሌሎች ክልሎችም ምሳሌ መሆን እንደሚቻል ግልፅ ነው።

በተጨማሪም ገጽታን መገንባት ነው በሚል በ2013 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ከብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን አመራሮች ጋር ቁጭ ብለን በእኛ የተቀረጸ ኢንሼቲቪ ነው። ይሄንኑ ኢንሼቲቭ ይዘን ወደ ተግባር ለመግባት ብቻችንን የምንሰራው ስላልሆነ የሲቪክ ማሕበራት አስተዋጾ ስለሚኖራቸው በአዋጁ ማጸደቅ ሂደትም በትግበራውም ከፍተኛ አስተዋጾ ሲያበረክቱ ስለነበር እነሱን ይዘን በአንድ በትንሽ ገለጻ ነው የጀመርነው።

ስንጀምር በጣም ትልቅ እናስባለን በትንሽ እንጀምራለን ከዚያም እያሰፋነው እንሄዳለን በሚል መርህ ነው። ስንጀምር አዲስ አበባ ውስጥም ቢሆን ሁሉም ክፍለ ከተማ በአንዴ አንጀምርም ብለን ወሰንን። ከዚያም ሁለት ክፍለ ከተሞች ቦሌና አራዳን መረጥን። በእነዚህ ክፍለ ከተሞች ከትምባሆ ጭስ ነጻ መሆን ያለባቸው የጤና ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች ቡና ቤቶችና ምግብ ቤቶች፤ ሆቴሎችና ካፍቴሪያዎች አሉ።

ቁጥራቸውም በጣም ብዙ ነው። ሁለተኛ በምሽትም ሆነ በቀንም ከፍተኛ የከተማ እንቅስቃሴ የሚበዛባቸው ቦታዎች ናቸው። ከክፍለ ከተሞቹም ሁሉንም ወረዳ መድረስ ስለማንችል ለዚህ በጣም ተጋላጭ የሆኑ ሶስት ሶስት ወረዳዎችን መረጥን። ሁለቱን ክፍለ ከተማ አንዳንድ የሲቪክ ማሕበር እንዲይዘው አደረግን። ከዚያ ዕቅድ አቅደን የሚሰራባቸው ቦታዎችን መረጥን።

ከመረጥን በኋላ ያስቀመጥነው ስትራቴጂ ለስራው የመንግሥት አካላት ብቻ ሳይሆን የግል ዘርፉም ባለቤት መሆን አለበት የሚል ነው። ስለዚህም መጀመሪያ የዳሰሳ ጥናት በመስራት ከሶስቱ ወረዳዎች ተቋማት መረጥን። የተወሰኑ ተቋማት በተለይም ጤና ተቋማት፣ ትምህርቤቶች፣ ቡና ቤቶች፣ ምግብ ቤቶችና ካፍቴሪያዎች መረጥን። ከዚያ የዳሰሳ ጥናቱ ተሰራ። ከዚያ በኋላ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ባሉበት ሪፖርት ቀርቦ ተገመገመ። ከዚያ ከ15 ቀን በኋላ ክትትል ተደረገ። መጀመሪያ በማስተማር ነው የጀመርነው። ከዚያ በኋላ ያሻሻሉ፣ ለውጥ ያመጡና በቁርጠኝነት የሰሩን ዕውቅና ሰጥተናል። በክትትሉ ወቅት እርምጃ መውሰድ ባለባቸው ላይ እርምጃ ወስደናል።

አሁን ስንመለከተው በሁሉም ከፍለከተማ ላይ እየተተገበረ ይገኛል። የሁሉም አመራርና የሕዝብ አጀንዳ ሆኗል። ንቅናቄ ተፈጥሯል። አሁን ስራውን ሙሉ በሙሉ በባለቤትነት ወስዶ የሚሰራው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው። ውጤታማ መሆን የተቻለው ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተዋናይ በማድረግ ነው። ትምህርት ቢሮ፣ ደንብ ማስከበር፣ ፖሊስ፣ ንግድና ራሱ ጤና ቢሮ የመሳሰሉ ተቋማትና አዲስ አበባ አስተዳደር በባለቤትነት ወስደው እንዲሰሩ፣ በዕቅድ እንዲመራ፣ ግብረ-ኃይል ተፈጥሮ በየጊዜው አፈጻጸሞችን እየገመገም ስለሄደ አሁን የምናያቸውን ውጤቶች እያየን እንገኛለን።

በቀጣዩን እትማችንን ሁለተኛው ክፍል ይዘን የምንቀርብ ይሆናል።

Tel : +251-11-552-41-22 | http://www.fmhaca.gov.et/contact/
+251-11-552-41-22 | E-mail contactefda@efda.gov.et
P.o.box. 5681 | Telegram channel link
Free call. 8482 | https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/